# የህጻናት መብቶች ለወጣት የቤት ዉስጥ ሰራተኛ

አዲስ አበባ ዉስጥ በወጣት የቤት ዉስጥ ሰራተኞች ስርጭት ላይ የተሰራ መጠነ-ሰፊ ጥናት ዋና ዋና ግኝቶች

ይህ ከ12-18 አመት የሆኑ 1371 ናሙና የቤት ዉስጥ ስራ ላይ የተሰማሩ ወጣት ሴቶች ላይ የተሰራ ጥናት ነዉ።

## በተባበሩት መንግስታት የህጻናት መብቶች ኮንቬንሽን ዉስጥ የተደነደጉ የህናጻት መብቶች፡

**አንቀጽ 19፡**
ከማንኛውም አይነት አካላዊ ወይም አእምሯዊ ጥቃት ጥበቃ የማግኘት መብት፣

**አንቀጽ 24፡**
አስፈላጊ የህክምና እርዳታ እና የጤና እንክብካቤ አቅርቦት ለሁሉም ህፃናት፤

**አንቀጽ 28፡**
ግዴታ የሆነዉን የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት በነፃ የመማር መብት፤

**አንቀጽ31፡**
የእረፍት እና የመዝናናት መብት

**አንቀጽ 32፡**
ከኢኮኖሚ ብዝበዛ፣ ከአደገኛ ወይም ከጎጂ ሥራዎች የመጠበቅ መብት፤

## የቤት ዉስጥ ወጣት ሴት ሰራተኞች ልምዶች፡

በአሰሪያቸው እጅ፣

**34%**
ወጣት የቤት ዉስጥ ሰራተኞች ስሜታዊ ሁከት ይደርስባቸዋል፤

**22%**
ወጣት የቤት ዉስጥ ሰራተኞች አካላዊ ጥቃት ይደርስባቸዋል፤

**20%**
ወጣት የቤት ዉስጥ ሰራተኞች አስፈላጊ በሆነ ግዚ መድሃኒት ወይም የጤና እንክብካቤ አይደረግላቸዉም፤

**54%**
የሚሆኑት ወጣት የቤት ዉስጥ ሰራተኞች በአሁኑ ጊዜ ትምህርታቸውን አይከታተሉም፤

በአማካይ በሳምንት ዉስጥ
**55**
ሰዓታት ይሰራሉ፤

**40%**
የሚሆኑት በሳምንት ውስጥ ያለ እረፍት በየቀኑ ይሰራሉ፤

**25%**
ለአደጋ ተጋላጭ በሆኑ ስራዎች እንዲሳተፉ ተደርገዋል፤

**85%**
የሚሆኑ እድሚያቸው ከ12-17 አመት ያሉት በከፋ የሕፃናት የጉልበት ብዝበዛ ውስጥ ነበሩ፤

THE FREEDOM FUND

POPULATION COUNCIL
Ideas. Evidence. Impact.

**የቤት ውስጥ ስራ በኢትዮጵያውያን ወጣት ልጃገረዶች እና ሴቶች ዘንድ ከተለመዱ የስራ ዓይነቶች ውስጥ አንዱ ነዉ።** ይህ ጥናት የተካሄደበት አካባቢ የተሰበሰበዉ መረጃ እንደሚያመለክተው ከቤት ዉስጥ ሴት ሰራተኞች 37 በመቶ የሚሆኑት ዕድሜያቸው ከ12-17 የሆኑ ወጣት የቤት ዉስጥ ሰራተኞች ናቸዉ። ከእነኚህ ወጣት የቤት ዉስጥ ሰራተኞች አብዛኞቹ የወር ደመወዛቸዉ አይከፈላችውም፤ 56 በመቶ የሚሆኑት ደግሞ አይቆጥቡም። ወጣት የቤት ዉስጥ ሰራተኞች የጉልበት ዋጋቸዉን ከመበዝበዛቸዉ በተጨማሪ ከትምህርት ገበታ ዉጪ ይደረጋሉ፣ በአሰሪዎቻቸዉ ቤት ዉስጥ እንዲቆዩ ይደረጋሉ፣ ከማህበራዊ ህይወት ይገለላሉ፣ እንዲሁም ከመጠን በላይ የቤት ዉስጥ ስራዎችን እንዲሰሩ ይደረጋሉ።[1]

**ወጣት የቤት ዉስጥ ሰራተኞች ብዙዉን ግዜ ለብቻ ቤት ዉስጥ እንዲሆኑ ይደረጋሉ። በተጨማሪም፣ በአሰሪዎቻቸዉ ላይ በተለያዩ ምክንያቶች ጥገኛ ይሆናሉ።ለምሳሌ ለቤት አገልግሎት፣ ለምግብ አገልግሎት እና ለገቢ ምንጭ ሲባል ጥገኛ ይሆናሉ።** ይህ ጥገኝነት፣ ልጆቹን ወደ ጎጂ የሥራ እና አስቸጋሪ የኑሮ ሁኔታ ይመራቸዋል።[2] ወጣት የቤት ዉስጥ ሰራተኞች ስለሚሰሩበት ቤት ቀጣሪዎቻቸዉ አሉታዊ ልምዶችን (ለምሳሌ አካላዊ እና ወሲባዊ ጥቃቶች) አይናገሩም፤ ምክንያቱም ይጎዱኛል የሚል ስጋት እና ገቢ ማጣት ዋነኛ ምክንያቶች ናቸዉ።

**ኢትዮጵያ የተባበሩት መንግስታት የህጻናት መብቶች ኮንቬንሽን ብታፀድቅም፣ ወጣት የቤት ዉስጥ ሰራተኞች ላይ ግልጽ የሆነ የመብት ጥሰት ይደርስባቸዋል።** አብዛኞቹ፣ እድመያቸው ከ12-17 ዓመት የሆናቸዉ ልጅ የቤት ዉስጥ ሰራተኞች ውስጥ 91 በመቶ የሚሆኑት የሕፃናት ጉልበት ብዝበዛ ዉስጥ ናቸዉ[3]፤ 85 በመቶ የሚሆኑት ደግሞ በጣም በከፋ የህናት የጉልበት ብዝበዛ1 ዉስጥ ይገኛሉ[4]። 20 በመቶ የሚሆኑት ደግሞ ሲታመሙ መድሃኒት አይሰጣቸዉም ወይም ወደ ህክምና አይወሰዱም። ከመጠን በላይ ለረጅም ሰዓት ማሰራት፣ የእረፍት እጦት እና ለአደገኛ የስራ ሁኔታዎች ተጋላጭነት ዋነኛ መንስዔ ናቸዉ።

**ወጣት የቤት ዉስጥ ሰራተኞች በተባበሩት መንግስታት የህጻናት መብቶች ኮንቬንሽን መሰረት በኢትዮጵያ ውስጥ ካሉ ሌሎች ልጆች ጋር እኩል መብት አላቸው።** ለወጣት የቤት ዉስጥ ሰራተኞች እና ለአሰሪዎቻቸዉ ግልጽ የሆነ የሚከተሉትን ነጥቦች ያካተተ ሕግ ያስፈልጋል፡ የተገደበ የስራ ሰዓት፣ ለእረፍት እና ለመማር በቂ ግዜ፤ ቀጣሪዎቻቸዉ እንደ አሳዳጊ ወይም ተንከባካቢ ሊወጧቸዉ የሚገቡ ኃላፊነቶች እና የመሳሰሉት ሕግ ሊወጣላቸዉ ይገባል። ወጣት የቤት ዉስጥ ሰራተኞች እንዲሰባሰቡ፣ ሕብረት እንዲመሰርቱና ግንኙነታቸውን እንድያጎለብቱ፣ የልጆች መብቶችና የአገልግሎት አቅርቦት ላይ ግንዛቤያቸዉን እንዲያሻሽሉ እና ለመተጋገዝና ችግሮቻቸዉን ለቀጣሪዎቻቸዉ የሚያደርሱበት ቦታ እና ስልቶች ሊመቻችላቸዉ ይገባል። በኢትዮጵያ የወጣት የቤት ዉስጥ ሰራተኞችን መብት ለማስጠበቅ የመንግስት ባለስልጣናት፣ ፖሊሲ አውጪዎች እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት የዚህ ጥናት ምክረ-ሃሳቦችን እንዲያጤኑ ጥሪ እናደርጋለን።

---

1 በአለም አቀፋ የሰራተኛ ድርጅት አጅግ በጣም የከፋ የህፃናት የጉልበት ብዝበዛ ስምምነት (C182) መሰረት።
2 በዚህ ጥናት ውስጥ የቤት ተግባራት ስራ፡ ምግብ ማዘጋጀት፣ ልብስ ማጠብ፣ ቤት ማጽዳት እና ህፃናትን ወይም የታመሙትን ወይም አዛውንቶችን መንከባከብ ያጠቃልላል።
3 ልጅ የቤት ዉስጥ ሰራተኞች እራሳቸውን እንደ የቤት ሠራተኛነት የገለጹትን እንዲሁም በሳምንት ከ14 ሰዓታት በላይ የቤት ውስጥ ሥራ የሚሰሩ እና ከአባትና ከእናታቸው ጋር አብረው የማይኖሩትን ልጃገረዶችን ያጠቃልላል።
4 በኢትዮጵያ የአሰሪ እና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 1156/2011ኢ.ም ድንጋጌዎች መሰረት።

# ምክረ-ሀሳቦች

- የቤት ውስጥ ስራ ዋና ዋና በሆኑ የሰራተኛ ሕግጋት ውስጥ እንዲካተትና የአለም አቀፍ የስራ ድርጅት ኮንቬንሽን 189ን ማፀደቅ፡
- ወጣት የቤት ዉስጥ ሰራተኞችን በማማከር፣ በመወከል እና ድምፅ በመሆን ጉዳዮቻቸዉ ወደፊት በሚወጡ ፖሊሲዎች እና የሕግ ዉሳኔዎች ዉስጥ እንዲካተት ማድረግ እና ማረጋገጥ።
- ለወጣት የቤት ዉስጥ ሰራተኞች እንከን የለሽና ቀልጣፋ የመለየት፣ የቅበላ፣ የመጠለያ እና የድህረ-እንክብካቤ አገልግሎቶችን ለማረጋገጥ የመንግስት፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን እና የማህበረሰብ መዋቅሮችን ትብብር መደገፍ።
- የወጣት የቤት ዉስጥ ሰራተኞችን በራስ መተማመን ችሎታቸዉን በመጨመር፣ መሰረታዊ የሕግ እና ፖሊሲ ግንዛቤዎችን በመስጠት፣ እንዲሁም ማህበራዊ ግንኙነታቸዉን በማሳደግ ወጣት የቤት ዉስጥ ሰራተኞች ላይ የሚደርሰዉን ማግለል እንዲቆም ማድረግ፤
- መሰረታዊ የትምህርት አማራጮችን ለምሳሌ የህይወት ክህሎት ስልጠና፣ ገንዘብ አያያዝና አጠቃቀም የመሳሰሉትን ለቤት ሰራተኞች በሚመች መልኩ ማዘጋጀት እና መስጠት፤

ይህ ጥናት ከአሜሪካ መንግስት ዲፓርትመንት ኦፍ ስቴትስ በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ የተዘጋጀ ነው። እዚህ የተገለጹት አስተያየቶች፣ ግኝቶች እና ድምዳሜዎች የጥናቱ ባለቤቶች እንጂ የአሜሪካ መንግስትን ሃሳብ አያንጸባርቁም።

Read the full report at **https://freedomfund.org/eth-cdw2022/**

**The Freedom Fund (Ethiopia Office)**
Mayswi Building 7th Floor
Ethio-China Ave
Addis Ababa
Ethiopia
+251 (0) 976 - 80 0506

**The Freedom Fund (US)**
315 Flatbush Avenue
#406
Brooklyn, NY 11217
USA
+1 929 224 2448

**The Freedom Fund (UK)**
Lighterman House
30 Wharfdale Road
London, N1 9RY
UK
+44 20 3777 2200

**Population Council**
One Dag Hammarskjold Plaza
New York, NY 10017
USA
+1 (212) 339-0500

**Population Council**
Heritage Plaza, 4th Floor
Cameroon Street
Addis Ababa,
Ethioia
+251 (0) 116-631712

The Freedom Fund is a United States 501(c)(3) public charity (EIN number 30-0805768).
The Freedom Fund UK is a company limited by guarantee registered in England and Wales (company number 08926428) and a registered UK charity (registration number 1158838).

www.freedomfund.org
info@freedomfund.org
@Freedom_Fund

October 2022